# ልዩነታቸው ምኑ ላይ ነው?

በዚህ ዓመት በግንቦት ወር ለሚካሔደው ምርጫ አመልክቶ በኢህአዴግና ተቃዋሚ ድርጅቶች መካከል የተጀመረው ክርክር ተከታትየ በኢህአዴግና ተቃዋሚዎች ያለው ***ልዩነቶች ምኑ ላይ*** መሆኑን ለመገንዘብ በቃሁኝ። ክርክሩን የተከታተለ ልዩነቱ ምኑ ላይ እንደሆነ ለመገንዘብ እንደቻለ እርግጠኛ ነኝ። ክርክሩ ብዙ ነገሮች ለማሳየት ችለዋል። የበኩሌን አመለካከት ***ልዩነታቸው ምኑ ላይ*** እንደሆነ ለመግለፅ ልሞክር። ስለ ክርክሩ አመልክቼ ብቻ አይደለም ስለ ኢህአዴግና ተቃዋሚዎቼ ሓሳብ ለመስጠት ለመመኮር የፈለግኩት። ከምርጫው በፊት በተለያዩ አጋጣሚዎች የታዘብኩትም ጭምር ግምት ውስጥ በማስገባት ነው ***ልዩነታቸው ምኑ ላይ*** እንደሆነ ሓሳብየን ለማስቀመጥ የተነሳሁት። ከዚህ በተጨማሪ አረጋዊ በርሀ ያመጣውን አዲሱ ወሬም የበኩሌን ሓሳብ ለማስቀመጥ እሞክራለሁ።

ያለኝን አስተያየት ከመስጠትየ በፊት ግን ለኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ለጀመሩት መልካም የድርጅቶችን ልዩነቶች ለሕዝብ የማስተዋወቅ ስራ ታላቅ ምስጋና ላቀብላቸው እወዳለሁ። እንዲሁም ለዓይጋ ፎረም (Aiga forum) ምስጋናየን ይድረስ እላለሁ። የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥንና ዓይጋ መልካም ስራ እየሰራቹህ ናቹህና ቀጡልበት።

ክርክሩ ላይ ብዙ ነገሮችን እየዳሰሰ አልፈዋል። በተቃዋሚ ድርጅቶች መሰረታዊ ችግሮች እንዳላቸው ክርክሩ እያሳየ መጥተዋል። ኢህአዴግ ኢትዮጵያን ለመምራት ዓቅም የላቹህም ብሎ ተቃዋሚዎቹን በተደጋጋሚ እንዲነግራቸው ሞክረዋል። አቶ ልደቱ ኢህአዴግ 17 ዓመታት በትግል ግዜ አሳልፋቹሃል። እኛም 18 ዓመታት ፖለቲከኞች ሆነን ቆይተናል። ዓቅሙ አለን ብለዋል። ለአቶ ልደቱ ማስተካከያ ኢህአዴግ የ35 ዓመታት ልምድ ነው ያለው። ዕድሜ ወሳኝ ነው ለማለት አይደለሁም ለመግለፅ የሞኮርኩት። ታሪክ ለመዛባት በትንሹ ስለሚጀምር አቶ ልደቱ ታሪክ ለማዛባት እየመከሩ ነው ለማለት እንኳን ባልችል አባባላቸው ግን ታሪክን በማዛባት ቦታ ስላለው ለማስተካከል ብየ ነው 35 ዓመታት ነው የኢህአዴግ የትግል ዘመን በማለት የአቶ ልደቱን አነጋገር ለማረም የመረጥኩት። ኢህአዴግ ኢትዮጵያን ለመምራት ዓቅም የላቹህም ሲል ምን ማለቱ ነው? በዕድሜ አልበሰላቹህም ማለቱ አይደለም። የድርጅታቹህን አመለካከት የድርጅታቹህን ዓላማ የድርጅታቹህን አጀንዳ ኢትዮጵያን ሊመራ አይችልም። ዓቅማቹህ ኢትዮጵያን ለመገንባት ለማሳደግ ሳይሆን ኢትዮጵያን ለማፍረስ ኢትዮጵያን ለመበታተን የደሃ ደሃ ለማድረግ የሚያስችል ዓቅም ነው ያላቹህ። ማለቱ ይመስለኛል ኢህአዴግ። የኢህአዴግ አባባል በፅኑ ትክክል ነው ብየ እቀበላለሁ። ምክንያቶቼን ልግለፅ።

1) ኢህአዴግ የሓይድሮ ኢሌክትሪክ ግድቦች ለመስራት ባሰበበትና በጀመረበት ግዜ ኢትዮጵያ የሓይድሮ ኤሌክትሪክ ግድብ መስራት አያስፈልጋትም ብለው የተቃወሙት የኢህአዴግ ተቃዋሚ ድርጅቶች ናቸው።

ይህንን አስተሳሰብ ያለው ድርጅት እንዴት ኢትዮጵያን ሊመራ ይችላል? አቶ ልደቱና ድርጅታቸው የ70 ዓመታት አርቆ እንደሚይስቡም ለመጥቀስ ሞክረዋል። የሰባት ዓመታት የኤሌክትሪክ ማመንጫ ስራ ጠቀሜታ ማየት ያልቻሉ እውነት የ70 ዓመታት የኢትዮጵያን ጥቅም ማየት ችለዋል ማለት ይሆን?

2) አቶ ልደቱ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የሱኳር በሽታ ነው የያዘው። ሲሉም ሰምቸ ነበረ። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መታከም አይቻልም። ኢትዮጵያ ከደህነት መውጣት አትችልም የሚሉ አመለካከት ያላቸው ሰዎች ወይም ድርጅቶች እንዴት ኢትዮጵያን መምራት ይችላሉ?

3) በቅርብ በአጋጠመውን የዓለማችን የኢኮኖሚ መቃወስ ያደጉ ሃገሮች ያንን ቀውስ ለመቋቋም እድገትን በመቀነስ ነው ብለዋል። ኢህአዴግ ደግሞ ዕድገትን በመቀጠል ነው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ማስተካከል የሚቻለው በአለበት ወቅት፡ ተቃዋሚዎች ያደጉ ሃገሮች ያላደረጉት እንዴት ኢትዮጵያ ታደርገዋለች? ምን ዓይነት ፍልስፍና ነው ብሎ ያሸፉ ሓይሎች በሌላ አነጋገር ነገሮችንና ሁኔታዎችን በመገንዘብ ትክክለኛውን መፍትሔ እንኳን ልያመጡ የቀረበላቸውን መፍትሔ ለማየት የሚሳናቸው ሓይሎች እንዴት ሃገርን ልያስተዳድሩ ይችላሉ?

ሶስቱ ነጥቦች የኢህ አዴግ ተቃዋሚ ድርጅቶች ኢትዮጵያን መምራት የማይችሉባቸት ከብዙ ምክንያቶች ጥቂቶቹ ናቸው።

አቶ ልደቱ የድሮ ስርዓት ናፋቂዎች ይለናል ኢህአዴግ። እኔ የድሮ ስርዓት አላውቀውም በታሪክ እንጂ። ብለዋል። የአፄ ሓይለስላሴ ስርዓት ላያውቁት ይችሉ ይሆናል አቶ ልደቱ። ኢህአዴግ የድሮ ስርዓት ናፋቂዎች ሲል የደርግም ስርዓት ጭምር ማለቱ አለመሆኑ በምን እንዳወቁ? የድርግን ስርዓት አቶ ልደቱ እንደሚያውቁት የዘነጉት አይመስለኝም። የዛን ስርዓት ናፋቂ ናቸው ማለት ይመስለኛል። የደርግ ስርዓት። በበኩሌ በዚህ የኢህአዴግ አባባል እስማማለሁኝ። የብሔር ብሔረ ሰብን እስከ መገንጠል የራስን መወሰን መብት አልቀበልም ሲሉ አቶ ልደቱና ድርጅታቸው የደርግ ስርዓት ስያራምደው የነበረውን የዓፈና ፕሮፓጋንዳ መድገም አይሆንም? የብሔር ብሔረሰቦችን መብት መረገጥ ሲኖር ብሔር ብሔረሰቦች ተቃውሞ ያመጣሉ። ተቃውሞ ስያመጡ ደግሞ ያ በስልጣን ያለውን ሓይል ጥያቄው ወይም ተቃውሞው ለማስታገስ ሓይል መጠቀሙን የግድ ይላል። ምናልባት ደርግ ከ19 ዓመታት በፊት ነበረ። ደርግ ላይመለስ ይችላል። በደርግ ወይንም ከደርግ በፊት የነበረውን የአገዛዝ ዘዴ ጭቆናና ጭፍጨፋ ግን ተመልሶ መምጣኡ የግድ ነው። እንድያውም በባሰ መልኩ። የኢዴፓና ሌሎች ድርጅቶች አካሔድም ያ የጭቆና ዘመን፡ ያ የዓፈና እና የጭፍጨፋ ዘመን እንድያውም በከፋ መልኩ እንዲመጣ የሚያደርግ አመለካከትና አካሔድ እያራመዱ ያሉት ድርጅቶች የድሮ ስርዓት ናፋቂዎችና ፈላጊዎች ካልተባሉ ታድያ ምን ተብሎ ይጠሩ? ካለፉት ስርዓታትስ በምን ይለያሉ? በእርግጥ እነዛ የዛን ስርዓታት ሰዎች አይኖሩም። በአዲስ ትውልድ ግን ያ ስርዓት ይደገማል ማለት አይደለምን?

የፌደራሊዝም አወቃቀር ኢህአዴግ እስካለ የሚሰራ። ኢህአዴግ ሲወድቅ አብሮት የሚወድቅ ነው። ሲሉም ሰምቻለሁ አቶ ልደቱና ኢንጂኔር ዘለቀ። ትክክል ነው አሁን ካሉት ድርጅቶች ስልጣን ላይ ቢመጡ። ያለውን የተጀመረውን አወቃቀር በምንም መልኩ አይኖርም። ለኢትዮጵያ መጥቀምና መምራት የሚችል ብቸኛው ድርጅት ኢህአዴግ ብቻ ስለሆነ ነው ያለውን አወቃቀር ኢህአዴግ እስካለ ብቻ የሚሰራው። ማንኛውም ድርጅት ኢትዮጵያን መጥቀም የሚችለው ባህሪውን መሰረት በማድረግ ነው። አንደኛው ህዝብ ለማስደሰት የሌላው ህዝብ መብት በመርገጥ የሚሉ ድርጅቶች ኢትዮጵያን አይጠቅሙም ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያን በከፋ መልኩ እንድትበታተንና እንደ ሃገር እንዳትቀጥል የሚያደርግ አካሔድ ያላቸው ድርጅቶች ናቸው የኢህአዴግ ተቃዋሚ ድርጅቶች። ባህርያቸው አይፈቅድላቸውምና።

ያለውን የፌደራሊዝም አወቃቀር ኢህአዴግን ባይኖር ሊሰራ ይችል ይሆናል። ብየ አስባለሁኝ። ኢህአዴግን በልጦ ለኢትዮጵያ መምራት የሚችል ድርጅት ቢፈጠር ኢህአዴግ ኢትዮጵያን ለመገንባት የሔደውን ጉዞ መንገዱን እንዳለ ተቀብሎ ቢሔድበት አመቺ ይሆንለታል። አሁን የተጀመረውን የፌደራሊዝም አወቃቀር ለኢትዮጵያ ዕድገትና ድህነትን ለመቅበር በአመቺ ሁኔታ እየፈጠረና ከግዜ ወደ ግዜ በይበልጥ ተጠቃሚው ህዝብ ለማገልገል በሚያመች ሁኔታ እየተዛመደ በመሔድ ላይ ያለውን አወቃቀር በመሆኑ ለኢትዮጵያ ጥቅም በቁርጠኝነት ከኢህአዴግ በላይ ሌላ ድርጅት ቢፈጠር በኢህአዴግ የተዘረጋውን የፌደራሊዝም መዋቅር ለማፍረስ የሚፈልግበት ምንም ዓይነት ምክንያት ስለማይኖረው ወደ ኋላ ተመልሶ አወቃቀሩ ላይ ለማስተካከል ግዜ የሚያጠፋበት ሁኔታ አይገጥመውም። እንደ ኢዴፓ ወይም ብርሃን ዓይነት ድርጅቶች ኢህአዴግን አሸንፎ ኢትዮጵያን ቢረከቡ እንኳን የትም መድረስ አይችሉም ብቻ ሳይሆን። ኢትዮጵያን እጅጉን ወደኋላ ይመልሱዋታል። ኢትዮጵያ እንደ ሃገር ሆናም የምትቀጥልበት ምንም ዓይነት ዋስትና አይኖራትም።

እንደ አቶ ልደቱና ድርጅታቸው የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት የሚነሳ አካሔድ ያለው ድርጅት ምን ግዜም ውድቀት ካልሆነ በስተቀር ሌላ የተሻለ ውጤት አይኖረውም። ሌላው የመብት ዓፈና እንይ ከአቶ ልደቱ አነጋገር። የጠ/ሚንስትሩ የግዜ ገደብ የለም ብለዋል። ኢህአዴግ በድርጅቱ ውስጥ የስራ ክፍፍል ስያደርግ ኢህአዴግ ይጠቅማል ባለው መንገድ እንጂ ከሌላ በመነሳት አይደለም። ማን ጠ/ሚኒስተር ይሁን? በሚለው ጉድይ ለኢህአዴግ የሚመለከት ጉዳይ ነው። አቶ ልደቱ ግን በኢህአዴግ የሚደረገውን የስራ ክፍፍል የኢህአዴግ ጉዳይ እያለ አቶ ልደቱ ከውጭ ሆነው ሊወስኑ በተደጋጋሚ ሞክረዋል። ምናልባት በድርጅታቸው ውስጥ ያንን ነገር ቢሞክሩት አይሻለም? አቶ ልደቱ በድርጅታቸው ውስጥ የሚኖረው የድርጅታቸው ሊቀ መንበር ለምን ያህል ዓመታት ማገልገል እንዳለበት ቢጨነቁ አይሻልም? ስለ ኢህአዴግ ከሚጨነቁ። ወይም የዓፈና ባህሪያቸው ይሆን እዛም እዛም የሚያዳርሳቸው?

አቶ ልደቱና ድርጅታቸው የብሔር ብሐረሰቦችን ጥያቄ አልተፈታም። ብለዋል። ከዛም በመነሳት ለነፃነት ጥያቄ ካነሱ ድርጅቶች አንድም ጥያቄውን የተወ የለም። ካለ ህወሓት በስተቀር ብለዋል። አሁንም አቶ ልደቱ ታሪክ እያዛቡ ነው ያሉት። ህወሓት ለመገንጠል የታገለ ድርጅት አልነበረም። ቢሔራዊ ጥያቄ ይዞ መነሳት መገንጠልን አያሳይም። ህወሓት መገንጠል ፍላጎቱ ቢሆን ኖሮ ማን ከለከለው? ለመሆኑ ብሔራዊ ጥያቄ ምን ማለት ነው? አቶ ልደቱና ድርጅታቸው ትርጉሙን በትክክል ያወቁት አይመስለኝም። ብሔራዊ ጥያቄ የሚመጣው በብሔሮች እኩልነት በማይኖርበት ግዜ ነው። ኢህአዴግ የብሔር ጥያቄ ተመልሰዋል ሲል ማንኛውም ብሔር ብሐረሰብ በእኩልነት መብቱ ተጠብቆ እንዲኖር ችለዋል። አንዱም ብሔር በሌሎች ላይ ሆኖ የሚጨቁንበት ግዜ አብቅተዋል። ማለቱ ነው። ለነፃነት ከተደራጁ አንዱም ጥያቄውን ያነሳ የለምስ ምን ማለት ነው? አቶ ልደቱና ኢዴፓ ኦነግን ለነፃነት የተደራጀ ሓይል ነው ማለት ይመስለኛል። የነፃነት ጥያቄ የሚመጣው ግን የተበደለ የተረገጠ የተጨቆነ ብሔር ወይም ብሔረሰብ ሲኖር ብቻ ነው። የነፃነት ጥያቄ አለ የብሔር ጥያቄ አሁንም አለ ካሉ አቶ ልደቱ ታድያ ምነው የጨቋኙና ተጨቋኙ ብሔሮች አንድ ሁለት ምሳሌ አላቀረቡም? በተጨባጭ የሚነገር አብነት የላቸውም።

ኢንጂነር ዘለቀ ሁሉም የኢህአዴግ ተቃዋሚ ድርጅቶች ትክክል አይደለም ያሉትን ነገር እንዴት ኢህአዴግ አይቀበልም። ለማለት ሞክረዋል። በ1966 ዓ/ም የተፈጠሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ኢህአፓ መኢሰን ሰደድ ኢጫድ ኢድዩ ህወሓት ኦነግ ግገሓት እነዚህ የተለያዩ ድርጅቶች የዛን ግዜ የህዝቡን ጥያቄ ለመመለስ ለትግል ሲዘጋጁና ትግልን ሲጀምሩ የተከተሉት የትግል ስልትና ዓላማ የሁሉም የተለያየ ነበረ። ህወሓት የሁሉም ድርጅቶች አካሔድ ስሕተት እንደሆነና ማስተካከል እንደሚገባው የበኩሉን አስተዋፆ ስያደርግ ለህወሓት አንድም የተቀበለው ድርጅት አልነበረም። ድርጅቶቹ ግን ብዙ ነበሩ። የተከተሉት ስልትና ስትራተጂ የተዛባና ስሕተት ስለነበረ አሁን እንደ ታሪክ ይነሳሉ። ወይም አለን የሚሉ እንጂ እስከ አሁን ለኢትዮጵያ ምንም ዓይነት ስራ አልሰሩም። ታድያ ብዛት መኖሩ ትክክለኛ ነገር ያስይዛልን? ብዙዎቹ ያሉትን ስሕተት እያለ ትክክል ነው ማለት ነበረበት ኢህአዴግ?

ኢንጂነር ዘለቀ ኢህአዴግ ከ18 ዓመታት በፊት ያወራው የነበረውን አሁንም እየደገመ ነው በማለት ሊተችቱት ሞክረዋል። ኢህአዴግ ከጅምሩ የተለያዩ አጀንዳዎች በየግዜውና በየሁኔታው የሚለዋወጡ ዓላማዎች ይዞ አልተነሳም። በስትራተጂ ይዞት የተነሳ ዓላማ በዚህ ግዜ ይለወጣል ተብሎ የተያዘ አልነበረም። ኢህአዴግ ያንን ዓላማ ለማስፈፀም ለወደፊትም ይቀጥልበታል። በሚቀጥሉት ዓመታትም ኢህአዴግ እንደድሮው ይህንን ዓላማ አስመልክቶ ተመሳሳይ ወረውን ይቀጥላል። ከጅምሩ ለትግል ያበቃው ዓላማ በፈለገው ምክንያት ኢህአዴግ አይለውጥም። ሌላው የኢንጂኔር ዘለቀ የተዛባ አመለካከት ኢህአዴግ 18 ዓመታት ሙሉ ያላደረገው እንዴት አሁን አደርጋለሁ ብሎ ይዋሻል? ብለዋል። ከ18 ዓመታት በፊት ኢትዮጵያ ምን ትመስል ነበር? በ18ቱ ዓመታትስ ኢትዮጵያ ምን ለውጥ አላት ብሎ መጀመርያ መታየት ያለበት ነገር ይመስለኛል። ኢትዮጵያ አሁን የደረሰችበት

ደረጃ የደረሰችው በኢህአዴግ አመራር እንጂ በሌላ ተአምር አለመሆኑ ማየት ያቃታቸው ለምንድነው ኢንጂኔር ዘለቀ? በፖለቲካ በኢኮኖሚ በማሕበራዊና ሌሎች ጉዳዮች ኢትዮጵያ ወደፊት እየተራመደች ያለችው በኢህአዴግ አመራር መሆኑን እነ ኢንጂኔር ዘለቀ ሊክዱት ይችላሉ። ወደዱም ጠሉም ግን ሓቂ በምንም ተአምር ማንም ዓይነት ሓይል ሊደብቀው አይችልም።

አቶ ለገሰ ቢራቱ (ቅንጅት) ዓንቀፅ 39 ኤርትራን ለማስገንጠልና ኢትዮጵያ የዓሰብ ወደብ እንዳይኖራት ለማድረግ ነው ኢህአዴግ ይህንን ሁኔታ የፈጠረው ብለዋል። እኔ አሁን በጣም እየገረመኝ መጥተዋል። እስከ አሁን ሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶች አንድ አዲስ ነገር ፈጥረው ኢትዮጵያን የሚጠቅም ነገር ስያወሩ አልሰማሁም። የ66ቱ ዓ/ም የብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄ ለማዳፈን የተደረገውን ዓፈና አሁንም እንዲመልሱት እንዲደግሙት ተደራጅተው ኢትዮጵያን ለመበታተን ውጣ ውረድ ማለታቸው ነው። አቶ ለገሰ ኤርትራን ለማስገንጠል ተብሎ ነው ዓንቀፅ 39 የተቀመጠው ብለዋል። ለምንድነው ኤርትራን ለማስገንጠል የተፈለገው? ኢህአዴግ በምን መልኩ ኤርትራ ስለተገነጠለች የዓሰብ ወደብ ባለመኖሩ ተጠቃሚ የሚሆነው? ብሎ ተንትነው ማስረዳት እንኳን አልቻሉም።

የፌደራሊዝም አወቃቀራቹህ ለኢህአዴግም አልተመቸም። ይላሉ። ኢንጂኔር ዘለቀ። ኢህአዴግ ያልተመቸውን ነገር ለምን ይመቻል ይላል? ኢህአዴግ እንኳን ይህንን የአሰራርና መስተዳድር ነገር ያለፈውን ስርዓት አልተመችንም ብሎ አልነበረም እንዴ ታግሎ መስዋዕት ከፍሎ ከስር መሰረቱ የጣለው። ታድያ አሁን ምን ተገኘ? ያልተመቸውን ተመችኝ የሚልበት ምክንያት ምን ተገኘ? ምነው ኢንጂኔር ሌላ በሰል ያለ የበለጠ ሓሳብ ብያፈልቁ አይሻልም።

ሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶች ፌደራሊዝም በኢትዮጵያ ተፈላጊ ነው ብሎ ተቀብለናል ብለዋል። መድረክ ኢዴፓ ቅንጅትና መኢብን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እንቃወማለን ብለዋል። ዓንቀፅ 39 እንደማይቀበሉ አስቀምጠዋል። በሌላው መልኩ ኢህአዴግ ያዋቀረውን ፌደራሊዝም የተማከለ ነው በማለት ይወቅሳሉ። የብሔር ብሔረሰብ መብት እየገደቡ እንደት ነው ተቃዋሚዎች ያልተማከለ ፌደራሊዝም ላይ የሚያምኑት? እንዴትስ ያልተማከለውን ፌደራሊዝም ይቀበላሉ? በፕሮግራማቸው ያለው ዓንቀፅ 39 አንቀበልም የሚሉትን ምን ማለት እንደሆነና ፌደራሊዝምና ያልተማከለ አስተዳደር ምን እንደሆነ በትንተናቸው በምንም ዓይነት አጥጋቢ ሓሳብ የላቸውም ብቻ ሳይሆን በጣም የተዛባና የተሳሳተ ነው። ፕሮፌሰር በየነ የመንግስት ረጅሙ ኢጅ በክልሎቹ፡ ከህዝብ ፍላጎት ውጭ መንግስት እንደፈለገው ሰዎችን ያወርዳል ይሾማል ብለዋል። ታድያ ኢህአዴግ የብሔር ብሔረሰቦችን የራስ የመወሰን ዕድል የተቀበለና ያከበረ ይህንን ካደረገ የብሔር ብሔረሰብ መብትን የተቃወምው መድረክ ዋናው መብት ገድቦ እንዴት ኢህአዴግን ይወቅሳል? መድረክና ኢዴፓ አቶ ልደቱና ፕሮፌሰር በየነና አቶ ለገሰ ቅንጅት እንዲሁም አቶ መስፍን መኢብን እንደተነተኑት ከሆነ ለብሔር ብሔረሰቦች የዕድሜ ልክ እስረኛ መብት እየሰጡዋቸው ነው ያሉት። ዕድሜ ልክ እስረኛ የመኖር መብት የመታከም የመናገር በዛ እስርቤት ውስጥ ሆኖ

የውጪውን ነገር የመከታተል መብት ኣለው። የተገደበ መብት ብቻ ነው ያለው። እስረኛው በሚፈፅመው ወንጀል ምክንያት እንዲህ ሲደረግ ብሔር ብሔረሰቦች ግን የሚታሰሩት ለምንድነው? ምን ወንጀል ቢፈፅሙ ነው መብታቸው በመድረክ በኢዴፓ በቅንጅትና በመኢብን መገደብ ኣለበት እየተባለ ያለው?

ኣቶ ልደቱ ኢዴፓ ኢህኣዴግ የጠየቅኩዋቸውን ጥያቄ ኣልመለሰሉኝም ይህንን ደግም የኢህኣዴግ የዓቅም ማነስ የሚያሳይ ነው ብለዋል። ነገሩ ግን ጥያቄው ስላልተመለሰ ኣይደለም ሁሉም በተቃዋሚ ድርጅቶች የቀረቡት ሓሳብና ጥያቄዎች ኢህኣዴግ በሚገባ መልሰዋል። ችግሩ ግን ኣቶ ልደቱ መልሱን የማስተዋልና የመቀበል ዓቅም ስላነሳቸው ይመስለኛል የተሰጣቸው መልስ ሊገባቸው ያልቻለው።

በሁለተኛው ዙር የተመለከትኩት ክርክር ኢህኣዴግና ተቃዋሚዎች ***ልዩነታቸው ምኑ ላይ*** እንደሆነ በሚገባ ለማየት ያስቻለ ነበረ። ብዙ ሰፋ ያለውን ነገሮች ለመዳሰስ ተሞክረዋል ብሁሉም ድርጅቶች። ዋናው ልዩነታቸው ባህሪያቸው ነው በኢህኣዴግና በተቃዋሚ ድርጅቶች ያለውን ልዩነት። ኢዴፓ መድረክ ቅንጅት ብርሃንና መኢብን ሁሉም በኣንድ ላይ ለኢትዮጵያ ኣንድነት የቆሙ በመምሰል የኢትዮጵያን ኣንድነት ለማፍረስ የተደራጁ ይመስላሉ። ለብሔር ብሔረሰቦች የሚሰጠው መብት የተገደበ ይሁን። ብሔር ብሔረሰቦች የራሳቸውን ዕድል የመወሰን መብት እንዳይሰጣቸው። ኣንዱን ብሔር ወይም ብሔረሰብ ሌሎቹን እንደፈለገው ቢጨቁናቸው ቢገዛቸው ሳይወዱ በግድ ኣሜን ብሎ መቀበል እንጂ መገንጠል የለባቸውም። በተገገርውና ገገርውን በሚፈጠረው ግጭት ወይም ጦርነት ኢትዮጵያ ተጠምዳ ትኑር። ለዘልኣለሙን ኢትዮጵያ ትጥፋ እያሉን ነው ያሉት። የሁሉም መብት በእኩልነት ሲከበር መፈቃቀር እንደሚኖር። መፈቃቀር ሲኖር ኣብሮ የመኖር ፍላጎት እንደሚኖር ተቃዋሚዎች በውል ማወቅ ነው ያቃታቸው። ኣሁን ተቃዋሚዎች እያሉት ያሉት ኣካሔድ እኮ ከኢህኣዴግ በፊት የነበሩ መንግስትታት ሰርተውበታል። ኢትዮጵያን ሲበታትን እንጂ ኣንድ ሲያደርግ ግን ኣልታየም።

ተቃዋሚ ድርጅቶችና ኢህኣዴግ በጣም ሰፊ ልዩነት ነው ያላቸው በኣተናተን ላይ። ተቃዋሚዎች እርስ በእርሱ የሚጋጭ ሓሳቦች ነው የሚያወሩት። ያልተማከለ ፌደራሊዝም እንቀበላለን ሲሉ በሌላ መልኩ ደግሞ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ኣያስፈልግም ይላሉ። ብሔር ብሔረሰቦች የፈለጉትን ለማድረግ ያልተማከለ ፌደራሊዝም ሳይሆን ተቃዋሚዎች እየተቀበሉት ያሉት የተማከለ መሆኑን ነው ትንተናቸው የሚያበራው። ትንተናቸው የሚለው በሌላ ትንተና ደግሞ ያፈርሱታል።

ሌላው ኢህኣዴግ የስራ ድርጅት ነው። ኢትዮጵያን ለማሳደግ በሚያደርገው ሁሉ ተቃዋሚዎችም ጭምር እንዲያውቁት የበኩሉ እየተዋጣና ከእነሱም ጋር እየተወያየ ለምሰራት ይሞክራል። ተቃዋሚዎች ግን እንኳን ሊሰሩ ኢህኣዴግ እንዳይ ሰራም መሰናከላቸው ሁሌ እንደዘረጉ ነው። ለሓይድሮ ኤሌክትሪክ

ግድቦች ግንባታ ከዓለም ባንክ ኢህአዴግ ብድር ሲጠይ በተቃዋሚዎች የተሰራውን ስራ ከበቂም በላይ ማስረጃ ነው።

በኢትዮጵያ ያለው ሕገ መንግስት ከሌላው ዓለም ልዩ ነው። ግትሩ ነው ወዘተ ተብለዋል በኣቶ ልደቱና ሌሎቹ ተቃዋሚ ድርጅቶች። ሃገራችን ዕርዳታ እንዳይሰጣት ብድር እንዳይሰጣት ሲሉ የተሰሙ የማንኛው መንግስት ተቃዋሚ ፓርቲዎች በዓለማችን አልታዩም። በፓርላማ ውስጥ ከመንግስት ጋራ የተቀመጡ ተቃዋሚ ሓይሎች። ለኢትዮጵያ ህዳሴ ምንም ያበረከቱት ነገር የለም ብቻ ሳይሆን ህዳሴው በስኬታማነት እንዳይቀጥልና እንዳይፋጠን ተደራጅተው እየሰሩ ያሉት ተቃዋሚ ድርጅቶች ናቸው። እነዚህ ድርጅቶች የኢህአዴግ ተቃዋሚ ድርጅቶች ሳይሆን መባል ያለባቸው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች ተብሎ ቢጠሩ ትክክል ይሆነል ብየ ኣምናለሁኝ።

ሌላው በዚህ ፅሑፍ ለማካተት ያሰብኩት ሓሳብ እንደሚቀጥለው ይሆናል።

ኣረጋዊ በርሀ የበረሃ ስሙ በሪሁ ከህወሓት እንደወጣ ጀምሮ እስከ ኣሁን የህወሓትን ስም ለማጥፋት ያልሸረበው ጉድ የለም። ልክ እንደ ኣበደ ውሻ ማረፍያ ኣጥቶ ብዙ ነገሮች ለመዳሰሰ ለማፍረስ ሞክረውል። ለመሆኑ ኣረጋዊ በርሀ ለምንድነው እንዲህ የሚሆነው? ራሱን ስለሚያውቀው ለመመለስ ግዜ ኣላጠፋም። ዶክተር ለመሰየም ያቀረበውን የሓሰት ምርምር በህወሓት ላይ ጉዳት ያደርስ ዘንድ ኣስቦ ይሆናል በሪሁ። እንደፈለገው ነገሮችን መለወጥ ግን ኣይችልም። እኔ ኣሁን ጠ/ሚንስተር መለስ በዛን ግዜ እንዲህ ኣለ ለማለት ኣይደለም የፈለግኩት። ከእነሱ ጋራ ኣልነበርኩም። ኣንድ የማውቀው ሓቅ ግን ኣለ። በድርቁ ግዜ ትግል ውስጥ ነበርኩኝ። በትግል ግዜ የነበርኩበት ምድብ በተለይ በድርቁ ግዜ ያንን ሓቅ እንዳውቅ ኣድርጎኛል። ኣረጋዊ በርሀ (በሪሁ)ና ገ/መድሂን ኣርኣያ (ኣቦይ ገ/መድሂን) በተለይ ኣቦይ ገ/መድሂን በጣም ነው የምንተዋወቀው። ኣቦይ ገ/መድሂን በ1976 ዓ/ም እስከ 1978 ዓዲ መሓመዳይ በተባለው ቦታ ነበር የሚኖሩት። ኣቦይ ገ/መድሂን ከመቸ ጀምሮ እዛ እንደነበሩ ኣላውቅም። እኔ ግን ከዛን ዓመት ጀምሮ ነበር በዛን ኣከባቢ የማውቃቸው ኣቦይ ገ/መድሂንን። እኔም ምድቤን እዛው ነበር። እንግዲህ እስከ 80 ዓ/ም በኣንድ ምድብ ነበር የቆየሁት። ያ ተገዛ የተባለውን የጦር መሳርያ ተገዝቶ መምጣት የነበረበት እኔ ወደ ነበርኩበት ምድብ ነው መምጣት የነበረበት። ምድቡ ትጥቅ ክፍል (09) ተብሎ ይጠራል። እኔ ያ ተገዛ የተባለውን ማወቅ ነበረብኝ። በፐርሰነልነት እዛው ምድብ ስሰራ ስለነበረ። እስከ 78 በሪጅን 1 እስከ 80 ደግሞ በህወሓት ዋናው የትጥቅ ክፍል ነበር በፐርሰነልነት የሰራሁት። ተገዝቶ ታድያ የት ሔደ? ይህንን መመለስ መቻል ያለባቸው ይመስለኛል። ኣቦይ ገ/መድሂን በዓዲ መሓመዳይ በነበሩበት ግዜ ኣረጋዊ በርሀ በህወሓት ኣመራር በነበረበት ግዜ የጦር መሳርያ ከተገዛ የመሳርያው ዓይነትና ብዛት ከየትኛው የጦር መሳርያ ነጋዴ ወንም ሃገር እንደተገዛ እንዴት ሳይገልፁት ቀሩ? የሚያውቁት ትክክለኛ ነገር ቢኖር።

ህወሓት ትጥቃችን ከጠላቶቻችን የሚለውን በጣም የሚያኮራ መፈክርና እምነት ነበረው። ትግሉ ተጀምሮ እስክያልቅ ድረስ ሻዕብያ ከሰጠን የመጀመርያው ጠመንጃዎች ሌላው በሙሉ ከደርግ በመስዋዕት የተገኘ ነበረ። መቸም በብዙ ጦርነቶች የደርግ የጦር ፕለይኖች ነበር በጣም አስቸጋሪ የነበሩት። ያንን ያህል ሚልየን ዶላር ለመሳርያ መግዥያ ቢውል ኖሮ መጀመርያ መግዘት የነበረብን የጦር ፕለይን ወይም የጦር ፕለይን የሚመታ ሚሳይል ነበር መጀመርያ መገዛት የነበረበት። ሌላም ታንኮችና ቢኤሞችም ጭምር መገዛት ነበረበት። ለመጀምሪያ ግዜ ህወሓት የቢኤም ባለቤት የሆነው 604ኛ ኮር በሽረ ከተደመሰሰ በኋላ ነው። ከዛም 605ኛ ኮር ሲደመሰስና 603ኛ በደብረታቦር ሲደመሰስ ነው ቢኤሞች የተገኙት። ደርግን በመደምሰሰና መስዋዕት በመክፈል የተገኘ ትጥቅ እንጂ እነ አረጋዊ በርሀና ገ/መድሂን አርኣያ እንዳሉት አይደለም ሓቁ።

በህወሓት ታሪክ ውስጥ ለመጀመርያ ግዜ የጦር ፕለይን የተመታቺው በ1977 ዓ/ም 8ኛው የደርግ ዘምቻ ባካሔደበት ማይሓንሰ በተባለው ቦታ ነው። ከ5 ዓመታት በኋላ በጉና ተራራ ነበር በተደጋጋሚ ፕለይኖች መምታት የተቻለው። እሱንም ቢሆን በ14.5mm ኣየር መቃወምያ ነበር።

ከድርቁ ከ2 ዓመታት በኋላ ማለት በ1979 ዓ/ም ክሳድ ጊመልና ካዛ በተባለውን ዋናው የህወሓት ቤዝ የህወሓት ኣመራር የነበሩበትና ዋናው የህወሓት የኣመራር ማእከል የነበረው ኣካባቢ በጦር ፕለይኖች ኣንድ ቀን ሙሉ ተብድበዋል። ያ ሰፈር ያለምንም ችግር ድብደባው ተከናውነዋል። በዛን 14.5mmና ዙ 23 ብቻ የኣየር መቃወምያ ነበር። ግን ምንም ሊፈይድ ኣልቻለም። ታድያ ህወሓት ለኣመራር ማእከሉ መጠበቅ ብሎ ለምን መሳርያዎቹን ኣላመጣም? በዛን ግዜ አረጋዊ በርሀ በክሳድ ጊመል ነበር ምድቡን በተደበደበው ሰፈር። እኛም ክሳድ ጊመል ነበርን ግን ኣከባብያችን ኣልተደበደበም። ግደይ ዘርኣፅየንም ካዛ በላይ ኤምዋን በማለት የተሰየመው በተደበደበው ኣከባቢ ነበረ። *<u>በ"ፅናት መፅሓፍ"</u>* ፀሓፊው ስዩም መስፍንና ኣባይ ፀሃየን ኣንድ ላይ እያሉ የጦር ፕለይኖች ደበደቡ ያለውን ያንን ደብዳብ ነው። በዛን ግዜም እኔ በትጥቅ ክፍል (09) ነበር ምድቤን።

ህወሓት መግዛት ከነበረበት የጦር መሳርያዎች ኣንዱ ኣየር መቃወምያ ነበረ። እንዲህ በትግሉና በትጥቅ ክፍል የነበርን ታጋዮች ያላወቅነው ትጥቅ ከተገዛ በህወሓት ውስጥ ኣልነበረም። ታድያ የት ገባ? ወይም ህወሓት የገዛው መሳርያ ኒዩክለር መሆን ኣለበት። እርግጠኛ ነኝ እነ ኣረጋዊ በርሀ ስለትናንሽ የጦር መሳርያ ኣይደለም እያወሩት ያሉት።

ቢቢሲና ኣረጋዊ በርሀ ምርጫውን ለማበላሸት ይጠቅማል ብለው ቆንጆ ነገር ኣገኘን ብሎ መመኮራቸው ከጠቀማቸው ይግፉበት። ኣረጋዊ በርሀ ከ77 ዓ/ም ወዲህ ሓቅን የማየት ዓቅሙን እየደከመ መምጣቱ ከስራው ከወሬው ለመገንዘብ ብዙም አስቸጋሪ ሆኖ ኣላገኘሁትም። የራሱን ስንፍና ትግልን ጥሎ መውጣቱ ማየት ሲገባው የራሱን ትቶ ስለሌሎች ያወራል።

ቢቢሲ ሓቅ የሌለውን ነገር እንዴት ሓቅ ነው ብሎ ያወራል? ጠ/ሚንስተሩ ያንን ጥፋት ሰርተው ኣሁንም ለጠ/ሚንስትርነት እየተወዳደሩ ነው በማለት ጉዳዩን ከምርጫው ለማያያዝ ሞክረዋል። ምክንያት ኣላቸው ኢህኣዴግ ቢመረጥ መለስ በጠ/ሚንስተርነት ይመረጣል። ጠ/ሚኒስተር መለስ ደግሞ በብዙ መልኩ በብዙ የዓለም ጉዳዮች ውጠታማ ስራ እየሰሩ ስለሆነ ያንን ደግሞ ለእነ ቢቢሲና ከጀርባ ላሉት ድብቆች ኣመቺ ሆነው ስላልተገኙ በሚቀጥለው ምርጫ ኢህኣዴግና ጠ/ሚንስተሩ መለስ እንዳይመረጡ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ ተብሎ የተጀመረ ዘመቻ ነው። እንጂ የእነ ኣረጋዊ በርሀ ትክክል ነገር ስለሆነ ነው ብሎ በማመን ኣይደለም ቢቢሲ ይህንን ለመደገፍ ታጥቆ የተነሳው።

ይሁን እንጂ ኢህኣዴግ በምንም መልኩ በምንም ምክንያት ህዝብ ለኣደጋ ኣጋልጦ የሰጠበት ግዜና ቦታ የለም። ህወሓት/ኢህኣዴግ ከህዝብ ውጭ መኖር ስለማይችሉ በህዝብ ላይ ለሚመጣው ጉዳት መስዋዕትም ከፍሎ ለመፍታት እንጂ ህዝብ ለኣደጋ ያጋለጡት በታሪክ የሚነሳ ኣንዳች ነገር ኣትገኝም።

እንግዲህ ለዛሬ እዚሁ ይብቃን።

ሃይለ/ተጋዳላይ
ኣውስትራልያ 09/03/2010
gedliweyn@yahoo.com